የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ጥር / 2012

አዲስ አበባ

## የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቱን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲት መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መጠረት ዓለማቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጠጋቢ የሆነ መረጋገጫ( የኦዲት አስተያየት )ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
የሰነድና ማህደር

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ**

1. የሙያ ደረጃዎችና የምዘና መሳሪያዎችን ለመከለስና ለማሰልጠን ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በተገባው ውል መሰረት ለተፈጸመው ክፍያ ወጪ የሆነ ብር 7,600,376.86 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ በመመዝገቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡
2. በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፀድቅ ብር 1,460,000.00 ለአማካሪ ድርጅት ተከፍሎ በመገኘቱ ክፍያው ለኤንሲው አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

3. በሂሳብ መደብ 4253 የተያዘ እና ለተለያዩ አቅራቢዎች በቅድሚያ የተከፈለ በድምሩ ብር 32,924,716.37 በወቅቱ ሳይወራረድ በመገኘቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲኖር እና ተሰብሳቢ ሂሳቦች የመሰብሰብ ዕድላቸው አነስተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

**ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ፤**

4. የመደበኛ በጀት ብር 15,281,667.25 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 103,409102.55 ሥራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

ከሠላምታ ጋር